የሰ/መ/ቁጥር 141978

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ - ሙሉተስፋ ከበደ

ተጠሪ፡- እዮኤል ተስፋዬ የሺጥላ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 114261 በቀን 22/02/09 የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 183790 በቀን 13/06/2009 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በዐቃቤ ህግ አማካኝነት የቀረበን ክስ ስለማንሳትና ከክርክር ውጭ ስለመሆን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ሁለት የወንጀል ክስ ያቀረበ ሲሆን ይኸውም የወንጀል ህግ ቁጥር 559/2/ እና 575 /2/ /ሀ/ የተመለከተውን ተላልፎ በዋናው መንገድ ለሚጓዝ ተሽከርካሪ ቅድሚያ በመከልከልና ያለጥንቃቄ ሲያሽከረክር

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-06155 ኢ.ት የሆነ መኪና የኋላ ግራ ጐን የገጨና አቅጣጫ እንዲስትና ከድንጋይ ጋር ተጋጭቶ በውስጡ የነበሩት የግል ተበዳይ አብነት ጉሹ በመኪናው አካል ተመትቶ የአንገት የቀኝ እግር እና የአካል ጡንቻዎች ላይ የህመም ስሜት እንዲሰማ ያደረገ እና እርዳታ ሳያደርግ በሌላ መኪና ገብቶ ያመለጠ በመሆኑ በቸልተኝነት ቀላል የአካል ጉዳት ያደረሰና በአደጋ ላይ የሚገኝ ሰውን አለመርዳት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ተጠሪ የቀረበው ክስ ደርሶት እምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ ከግል ተበዳይ ጋር የታረቀ መሆኑን የገለፀ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይህንኑ ገልጾ በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በወንጀል ህግ ሥ/ሥርዓት ቁ 151/2/ መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሳይቀበል መዝገቡን ዘግቶቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በተጠሪ ላይ የቀረበው የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ በወንጀል ህግ 212 መሠረት በግል አቤቱታ የማይቀርብና በወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት በእርቅ ሊነሳ የማይችል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክሱን ያቋረጠው መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ የቀረበ ክስ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት በእርቅ በመጨረስ የሚቋረጥ መሆኑን ለመመርመር ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ታዞ በሰጠው መልሱ በወቅቱ እኔም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብኝ እራሴን ለማዳን ወደ ህክምና ተቋም ሄጃለሁ ሆነ ብዬ ሰውን ላለመርዳት አልሄድኩም ብሎ ክሱን በመካድ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪም ዕርቁን የማይቃወም መሆኑን እና የሚያቀርቡት ማስረጃ እንደሌለ በመግለጽ ፍ/ቤቱ ክሱን አቋርጧል እንጂ የግል አቤቱታ ነው በማለት አይደለም፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይጽናልኝ ብሏል፡፡ አመልካች በሰጠው የመልስ መልስም ሁለቱም ክሱ የተቋረጠው በእርቅ እንጂ አመልካች ማስረጃ ባለማቅረቡ ወይም እንደክሱ ባለማስረዳቱ አይደለም የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/3/ የተመለከተውን ተቃውሞ አላነሳንም እንጂ በሁለተኛው ክስ ላይ ተቃውሞ ገልፀናል፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ ክሱን ማቋረጡ ተገቢ አይደለም በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነው በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ክሶችንና የሚቀርቡበትን አግባብ የሚመለከት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ ከቀረበው ጭብጥ አንጻር የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ሀ/ በወንጀል ህግ ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት ከተበዳዩ ጋር በዕርቅ በመጨረስ ክሱ የሚቋረጥ ስለመሆኑ አለመሆኑ ምላሽ የሚሰጥ ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የወንጀል ህግ ግብ ስለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የሀገሪቱን መንግስት የህዝቦችን የነዋሪዎቹን ሰላም ደህንነት ሥርዓት መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡ መንግስት በህዝብ ስም ሆኖ ለዜጐች ተወክሎ የወንጀል ጉዳይን እንዲከታተልና ክሶ እንዲያስቀጣ ኃላፊነት ሊወድቅበት የቻለውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ሆኖም የጠቅላላውን ህዝብ ሰላምና ፀጥታ የሚያደፈርሱ ከተጐጂው ሠው ጥቅም በላይ አልፈው የሌሎችን ጥቅም የማይነኩ አሉ፡፡ በእርግጥ በጠቅላላው ተበዳይ ቢስማማም ባይስማማም የወንጀል ክስን መከታተል የመንግስት ኃላፊነት ቢሆንም በእነደዚህ ባሉ ነገሮች የተጐዳው ሠው ጉዳዩን ክሶ በፍርድ እንዲታይለት ፈቃደኛ መሆኑ በእርግጥ ካላሳየ በቀር መንግስት ይህንን ግዳጁን አያከናውንም፡፡

የወንጀል ህጉ ክስ በቀረበ ጊዜ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች የሚገልጽ የተጠናቀቀ ዝርዝር አይገልጽም ፡፡የወንጀል ህግ አንቀጽ 212 ቢሆንም በጠቅላላው መልክ ነው በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ውስጥም የሚገኙ ድንጋጌዎች “ማናቸውም … የግል አቤቱታ በቀረበ ጊዜ …. ይቀጣል” ሲል ያዛሉ፡፡ እነዚህን አንቀጾች በመተላለፍ ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ በግል አቤቱታ እንዲያቀርብ ከተፈቀደለት ሰው በቀር በሌላ በማንም ሠው የክስ ጉዳይ ሊንቀሳቀስ አይችልም፡፡ የግል ከሳሹ የክሱን ማመልከቻ ካዘጋጀ በኋላ የክሱ ጉዳይ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 150-153 በተገለፀው መሠረት ይመራል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በአመልካች በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት ክሶች 1ኛ የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/2/ እና 2ኛ የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ በግል ተበዳይ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ አማካኝነት የሚቀርቡ ወይም እንዲቀርቡ የታዘዙ ክሶች አይደሉም፡፡ ክሱም በስር ፍርድ ቤት የቀረበው በአመልካች /በመንግስት/ በዐቃቤ ህግ ነው፡፡ ክሱን የሚመራው

በወ/ህ/ሥ/ሥ /ቁ 132-135 ፣ 185፣196፣117፣ 94-98፣ 123-131 እና 136-149 በተመለከቱት መሠረት ይሆናል፡፡

ስለሆነም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበውን የወንጀል ክስ የግል ተበዳይ ክሱን ትቷል በማለት በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 151/3/ መሠረት በግል አቤት ባይ የቀረበ ክስ በሚመራበት ሥነ ሥርዓት የወንጀል ክሱን ያቋረጠው የወንጀል ህግን ግብ እና በዓቃቤ ህግ ስለሚቀርቡ የወንጀል ክስ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ክስ አመራር ያልተከተለ በመሆኑ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንን ሳያርም ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 114261 በቀን 22/02/09 የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 183750 በቀን 13/06/2009 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ሀ/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች የቀረበውን ክስ ተጠሪን አስቀርቦ የወንጀል ክሱን በመስማት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /መ/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**